የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE
# OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፺
አዲስ አበባ መስከረም ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 90
ADDIS ABABA, 23rd, September, 2019

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፩/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ........................................ገጽ ፲፩ሺ፯፻፺፬

**CONTENT**

PROCLAMATION NO.1161/2019

Expropriation of Land holdings for Public Purposes, Payments of Compensation and Resetlement of Displaced People Proclamation……………………………………………….Page 11794

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፩/፪ሺ፲፩

## ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ

መንግስት ለሕዝብ አገልግሎት ለሚያከናውናቸው የልማት ሥራዎች መሬትን መጠቀም አስፈላጊ ስለሆነ፤

የአገሪቱ ከተሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉና የነዋሪዎቹም ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ በከተሞች ፕላን መሠረት ለመኖሪያ ቤት ግንባታ፣ ለመሠረተ ልማት፣ ለኢንቨስትመንትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውል የከተማ መሬትን መልሶ ማልማት አስፈላጊ በመሆኑ፣እንዲሁም በገጠር ለሚከናወኑ የልማት ሥራዎች መሬት አዘጋጅቶ ማቅረብ በማስፈለጉ፤

የመሬት ይዞታ እንዲለቅ ለተደረገ ባለይዞታ ተገቢና ተመጣጣኝ ካሣና የተነሽ ድጋፍ ለመክፈል ግምት ውስጥ መግባት የሚገባቸውን መሠረታዊ መርሆዎችን ለይቶ መወሰን በማስፈለጉ፤

**PROCLAMATION NO.1161/2019**

## A PROCLAMATION TO DETERMINE EXPROPRIATION OF LANDHOLDINGS FOR PUBLIC PURPOSE, PAYMENTS OF COMPENSATION AND RESETLEMENT

**WHERE AS,** it is necessary that government needs to use land for development works it carries out for public services;

**WHEREAS,** land expropriation has become necessary to address the steadily growing urban population which requires more land for building houses, infrastructure; and for redevelopment of the urban slams to invigorate investment and other services; and for development activities in rural areas;

**WHEREAS,** it is essential to determine the types of compensable properties and lost economic interests and the principles thereof and establish the methods of valuation in order to pay land holders whose landholdings and property are expropriated or damaged or lost their economic interests in the

ካሣውን የመተመን፣ የመክፈል እና ተነሺዎችን መልሶ የማቋቋም ሥልጣንና ኃላፊነት ያለባቸውን አካላት በግልጽ ለይቶ ለመወሰን በማስፈለጉ፤

በነባሩ ሕግ ያጋጠሙ የሕግ ክፍተቶችን ለማስተካከልና ሌሎች የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና ካሣ የሚከፈልበት ሥርዓቱን ይበልጥ ውጤታማ የሚያደርጉ ድንጋጌዎችን ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከይዞታ መነሳትና ካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ ስለሚኖር የቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት በግልጽ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፌደራል መንግሥት የመሬት አጠቃቀም ሕግ የማውጣት ሥልጣን እንዳለው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ ፶፩(፭) በመደንገጉ፣ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ ንብረትን በሚመለከት ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ እንዲከፈል በአንቀጽ ፵(፰) በመደንገጉ እንዲሁም ተነሺዎች በመንግስት ዕርዳታ እንዲቋቋሙ በአንቀጽ ፵፬(፪) የተቀመጠውን መሠረተ ሀሳብ በዝርዝር መደንገግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፪)(ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፩/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

process of expropriation fair and equitable compensation;

**WHERE AS,** it is necessary to identify and define the powers and responsibilities of authorities which are in charge of property valuation; payment of compensation and resettlement;

**WHEREAS**, it is necessary to rectify and fill gaps envisaged in the former law and to include other provisions to make the system of expropriation of land holdings and payment of compensation more effective;

**WHERE AS,** it is necessary to determine the decision making process and grievances procedure related with the expropriation and payment of compensation ;

**WHEREAS,** it is necessary to enact detailed laws to implement the general powers given to the Federal Government under the Constitution of Federal Democratic Republic of Ethiopia to enact laws regarding land use under Article 51(5); and Expropriate of Private property for Public Purposes and payment of fair and equitable compensation to the expropriated land holders under Article 40(8) and provide support to resettle displaced people under Article 44 (2);

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (2) ( a) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the"Expropriation of Land holdings for Public Purposes, Payments of Compensation and Resetlement Proclamation No. 1161/2019".

## ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

፩/"የህዝብ ጥቅም" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማጎልበት የክልል ካቢኔ፤ የአዲስ አበባ፤ የድሬዳዋ ወይም አግባብ ባለው የፌደራል አካል በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ወይም በልማት ዕቅድ ወይም በመሠረተ ልማት መሪ ፕላን መሠረት ለሕዝብ የተሻለ የጋራ ጥቅምና ዕድገት ያመጣል ተብሎ የተወሰነው ነው።

፪/"የንብረት ካሣ" ማለት የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ ለሚወሰንበት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ለሰፈረው ንብረት ወይም ላደረገው ቋሚ ማሻሻያ በዓይነት ወይም በገንዘብ ወይም በሁለቱም የሚከፈል ክፍያ ነው።

፫/"የልማት ተነሽ ካሣ" ማለት ባለይዞታው የመሬት ይዞታውን ሲለቅ በመሬቱ ላይ የመጠቀም መብቱ በመቋረጡ ምክንያት የሚደርስን ጉዳት ለማካካስ የሚከፈል ክፍያ ነው።

፬/"የልማት ተነሽ ድጋፍ" ማለት የመሬት ባለይዞታ ከመሬቱ በጊዜያዊም ሆነ በቋሚነት ሲነሳ ከአዲሱ አካባቢ ጋር መላመድ እንዲችል ከንብረት እና ከልማት ተነሽ ካሣ በተጨማሪ በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ ድጋፍ ነው።

፭/"የኢኮኖሚ ጉዳት ካሣ" ማለት ከቦታቸው ያልተነሱ ነገር ግን መሬት ለሕዝብ ጥቅም በመለቀቁ ምክንያት በመቀጠር ወይም በመነገድ ወይም በማከራየት እና ከመሳሰሉት ያገኙት የነበረ ገቢ በመቋረጡ ለሚደርስ ጉዳት የሚከፈል ካሣ ነው።

፮/"የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና ሥነ-ልቦና ጉዳት ካሣ" ማለት ለተነሺ ከነበረበት አካባቢ በመነሳቱ የነበረው ማህበራዊ ትስስር በመቋረጡ የሚከፈል

## 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/"Public Purpose" means decision that is made by the cabinet of a Regional State, Addis Ababa, Dire Dawa or the appropriate Federal Authority on basis of approved land use plan or; development plan or; structural plan under the belief that the land use will directly or indirectly bring better economic and social development to the public;

2/"Property Compensation" means, payment to be made in cash or in kind or in both to a person for his property or permanent improvements situated on his expropriated landholding;

3/ "Displacement Compensation" means payment to be made to a land holder for the loss of his use right on the land as a result of expropriation;

4 / Displacement Assistance" means payment to be made, in addition to property and displacement compensations, for a landholder who permanently or temporarily displaced in order to help him adjust to the new place;

5/"Economic Loss Compensation" means payment to be made to those who are not displaced but who suffer loss of employment, trade; or rentals, or similar activities as a consequence of expropriation of land for public purposes;

6/"Social Ties Discontinuance and Moral Damage Compensation" means payment to be made to displaced people for the breakup of their social ties and moral

የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ እና የሥነ-ልቦና ጉዳት ማካካሻ ክፍያ ነው፡፡

፯/"መልሶ ማቋቋም" ማለት ለልማት ተብሎ በተወሰደው መሬት ምክንያት የሚያገኙት ጥቅም ለሚቋረጥባቸው ተነሺዎች ዘላቂ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው የሚሰጥ ድጋፍ ነው፡፡

፰/"ቀመር" ማለት ለህዝብ ጥቅም በሚለቀቅ መሬት ላይ ለሠፈረ ንብረት ወጥ የሆነ የካሣ ስሌት የሚሰራበት ዘዴ ነው፡፡

፱/"ቋሚ ማሻሻያ" ማለት በይዞታው ላይ የምንጣሮ፣ ድልደላና እርከን ሥራ፣ ውሃ መከተር ሥራ እና የግቢ ንጣፍና ማስዋብ የመሳሰሉትን ሥራዎች ያጠቃልላል፡፡

፲/"የማቋቋሚያ ማዕቀፍ" ማለት ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከመሬት ይዞታቸው እንዲነሱ ሲደረግ ዘላቂ የሆነ የገቢ ምንጭ ሊኖራቸው የሚያስችል የሥራ መርሐ ግብር ነው፡፡

፲፩/"የወል ይዞታ" ማለት ከመንግሥት ወይም ከግል ይዞታነት ውጭ የሚገኝና የአካባቢው ማህበረሰብ ለግጦሽ፣ ለደንና ለማህበራዊ አገልግሎት በጋራ የሚጠቀሙበት የመሬት ይዞታ ነው፡፡

፲፪/"ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ነው፡፡

፲፫/"የከተማ አስተዳደር" ማለት በሕግ የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው፡፡

፲፬/"መሠረተ ልማት" ማለት ከመሬት በላይ ወይም ከመሬት በታች ያለ መንገድ፣ የባቡር ሀዲድ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የመስኖ፣ የውሃ መስመር ወይም የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ሲሆን ሌሎች ተያያዥ ግንባታዎችንም ይጨምራል፡፡

damage suffered;

7/“Resettlement” means support provided to people who are not physically displaced but lost their economic benefit due to expropriation of land for public purposes and so as to enable them generate sustainable income.

8/“Valuation ” means a common compensation valuation method used to calculate the value of property on expropriated land;

9/“Permanent Improvement” means improvements made permanently to the land like clearing, leveling and terracing the land, including the costs of water reservoir and other agricultural infrastructure and urban courtyard floors and other decoration works.

10/“Resettlement package” means work program to people whose landholding is expropriated for public purpose so as to enable them generate sustainable income;

11/“Communal landholding” means land which is neither state owned nor individually held; and which is held and used by communities for grazing, forestry, and other social services, etc;

12/ "Region" means any region referred to in Article 47(1) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution;

13/“Urban administration" means an organ to which urban administrative powers and duties have been given by law;

14/“Infrastructure” means road, railway, airport, telecommunication, electric power, irrigation, water supply line or sewerage line found on or below the ground and includes other related constructions.

፲፭/"የአገልግሎት መስመር" ማለት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ መሬት ከመሬቱ በላይ ወይም ውስጥ የተዘረጋ የውሃ፣ የፍሳሽ፣ የኤሌክትሪክ ወይም የስልክ መስመር ሲሆን ሌሎች ተመሳሳይ ስራዎችንም ይጨምራል።

፲፮/"ተነሺ" ማለት ለሕዝብ ጥቅም መሬት በሚለቀቅበት ጊዜ በተለቀቀው መሬት ላይ ይኖር የነበሩ ባለይዞታ፣ ተከራይ፣ ተቀጥሮም ሆነ በግል ይሰራ የነበረ፣እና በጥገኝነት ይኖር የነበረን ያጠቃልላል።

፲፯/"አቤቱታ ሰሚ" ማለት በዚህ አዋጅ አፈፃፀም ላይ ለሚነሳ ቅሬታ የሚመለከት እና ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው።

፲፰/"ይግባኝ ሰሚ" ማለት አቤቱታ ሰሚ አካል የሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ተመልክቶ ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው።

፲፱/"እውቅና ያለው ገማች" ማለት ቋሚ ንብረቶችን ለመገመት አግባብ ባለው አካል እውቅና የተሰጠው ገማች አካለ ነው።

፳/"አስቸኳይ ልማት" ማለት በመደበኛው የጊዜ ሰሌዳ መሄድ የማይችልና ለከፍተኛ ወጪ ሊዳርግ ወይም ከፍተኛ ገንዘብ ሊያሳጣ የሚችል መሆኑ ተረጋግጦ በመንግስት የተወሰነ የልማት አይነት ነው፣

፳፩/"ውስብስብ መሰረተ ልማት" ማለት በተለመደው አሰራር የማይሰራ፣በአገር ውስጥ ባለው ባለሙያ የማይሰራ፣ እቃዎችም በክምችት የማይያዝበት፣ ከአገር ውጪ ግዥ የሚጠይቅ እና መሰል ስራ ሆኖ በመሰረተ ልማት ባለሙያ የተረጋገጠ እና በመሰረተ ልማት ተቋም ሀላፊ የፀደቀ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልገው የመሰረተ ልማት አይነት ነው፣

15/ "Utility line" means water, sewerage, electric or telephone line existing on or under a land to be expropriated for public purpose;

16/"Displaced People" means a person,households,firms,or public or private institutions who has been living in occupied land,including tenants,employed and self-employoyed persons on the land for public benefit,

17/" Complaint Hearing Body" means the body that deals with and resolves complaints about the implementation of this Proclamation.

18/"Appeal body" means a body that reveiws the decision g iven by a compliant hearing body and pass its decision.

19/"Recognized Evaluater" means an evaluator that has been accredited by the appropriate body for the estimation of fixed assets.

20/Urgent Development" means a development which does not be implemented by the normal schedule and which the government ensures it as costly or potentially costly.

21/ Complex Infrastructure" means infrastructure which can not be done as usual ,can not be done by the country's professionals, where goods are not stored, requires purchasing abroad, and a similar act proved by an infrastructure expert and approved by the Head of Infrastructure Institution and is type of infrastructure that needs more time.

፳፪/"ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ፋይዳ ያላቸው ልማቶች" ማለት ለኢትዮጵያ እድገትና ትራንፎርሜሽን ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጡ የልማት ፕሮጀክቶች ወይም የትብብር መስኮችን ለማስፋት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሀገሪቱ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ለሚኖራት የተሻለ ግንኙነት መሰረት እንዲጥሉ የታቀዱ ልማቶች ናቸው።

፳፫/ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

፳፬/ማንኛውም በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

፫. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን፣ ካሣ የሚከፈልበትንና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ በሚመለከት በመላ ሀገሪቱ በከተማም ሆነ በገጠር ተፈጻሚ ይሆናል።

፬. **መርሆዎች**

፩/የመሬት ይዞታ ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ የሚደረገው በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ወይም በከተሞች መዋቅራዊ ዕቅድ ወይም በመሠረተ ልማት መሪ ፕላን መሠረት መሆን አለበት።

፪/ለሕዝብ ጥቅም መሬት ሲለቀቅ የሚከፈል ካሣና የሚሰጥ የማቋቋሚያ ድጋፍ የተነሺዎችን የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽልና የሚያስቀጥል መሆን አለበት።

፫/ በፌደራል መንግስትም ሆነ በክልል መንግስታት፤በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ለሚከናወኑ የልማት ሥራዎች በአንድ አካባቢ ለሚገኙ ቦታዎች ለሠፈረ ንብረት እና ተጓዳኝ ጥቅም ማጣት የሚከፈል የካሣ ነጠላ ዋጋ ተመን ተመሳሳይ መሆን አለበት።

22/"Development of National or Regional Significance" means a development that is intended to bring great chanage on the bases of development projects or creat better relations with other countries through development projects or activities to promote change in Ethiopia.

23/"Person" meanS any natural or legal person.

24/Any expression in the Masculine gender includes the Feminine.

3. **Scope of Application**

This Proclamation shall apply throughout the country in rural and urban centers in matters relating to land expropriation; payment of compensation; and resettlement of landholders whose land is expropriated for public purpose.

4. **Principles**

1/ Expropriation of land for public purposes shall be made only on the basis of approved land use plan; urban structural plan; or development master plan.

2/Compensation and resettlement Assistance Compensation for the expropriated land shall sustainably restore and improve the livelihood of displaced people.

3/The amount of compensation to be paid at Federal, or Regional or Addis Ababa or DireDawa level for similar properties and economic losses in the same areas shall be similar.

፬/ለሕዝብ ጥቅም መሬት እንዲለቀቅ ሲደረግ አሰራሩ ግልጽ፣አሳታፊ፣ ፍትሃዊ እና ተጠያቂነትን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

4/Where land is expropriated for public purpose, the procedure shall be transparent, participatory,fair and accountable.

## ክፍል ሁለት

## መሬት ለማስለቀቅ ስለሚፈፀም ሥነ-ሥርዓት

## Part II

## Procedure to Expropriate Land

### ፭.የሚለቀቀው መሬት ለሕዝብ ጥቅም መሆኑን ስለመወሰን

### 5. Decision on Expropriation for Public Purpose

፩/አግባብ ያለው የፌደራል አካል ወይም የክልሉ፤አዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ካቢኔ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተሻለ ልማት ያመጣል ብሎ በመሬት አጠቃቀም እቅድ ወይም በልማት እቅድ ወይም በመሠረተ ልማት መሪ ፕላን መሠረት የሚለቀቀውን መሬት ለሕዝብ ጥቅም መሆኑን ይወስናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ መሠረት ለመወሰን መሪ ፕላኑ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ፕላን ሊኖረው ይገባል፡፡

፫/ለሕዝብ ጥቅም መሬት እንዲለቀቅ ሲወሰን ለካሣ እና መልሶ ማቋቋም የሚያስፈልግ በጀትና በጀቱ በማን እንደሚሸፈን አብሮ መወሰን አለበት፡፡

፬/የመሬት ባለይዞታዎች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተገለፀው መስፈርት ሳይሟላ መሬታቸው ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ የሚሰጥ የሕዝብ ጥቅም ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

፭/የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም እንደ አስፈላጊነቱ የክልሉ፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ካቢኔ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ማስለቀቅ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣኑን ለከተማ ወይም ለወረዳ አስተዳደሩ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

1/ The appropriate Federal Authority, or a Regional, Addis Ababa, Dire Dawa cabinet shall decide on the basis of an approved land use plan; or master plan; or structural plan whether the expropriated land directly or indirectly brings better development and is beneficial to the public.

2/The Master Plan; referred under sub article 1 of this Article shall have detailed action plan.

3/The budget necessary to cover the costs of compensation and resettelemnt and the responsible body that shall cover these costs shall be made clear at the time when expropriation for public purpose is decided.

4/ Land holders may file objections on the public purpose decision where their land is expropriated in the absence of the fulfillment of the requirements provided under sub articles (1) and (2) of this Article.

5/ Not with standing to sub article 1 of this Article, a Regional፣ Addis Ababa, Dire Dawa cabinet may delegate a Woreda or City Administration to decide on land expropriation for public purpose.

**፮.መሬት የማስለቀቅ ሥልጣን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ መሠረት ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ ውሳኔ የተሰጠበትን መሬት የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር መሬቱ የማስለቀቅ እና የመረከብ ሥልጣን አለው።

**፯.ለባለይዞታዎች ቅድሚያ የማልማት መብት ስለመስጠት**

፩/በከተማ ለመልሶ ማልማት በተከለለ ቦታ ውስጥ ያለ ባለይዞታ በፕላኑ መሠረት ይዞታውን በግልም ሆነ በጋራ ቅድሚያ የማልማት መብት አለው።

፪/የገጠር መሬት ባለይዞታ ለእርሻ ስራ የሚለቀቅ ሲሆን አቅሙ ካለው ይዞታውን በግልም ይሁን በቡድን በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ መሠረት ቅድሚያ የማልማት መብት አለው።

፫/በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሰረት ለተነሺው ቅድሚያ የማልማት መብት የሚጠበቅለት በፕላኑ መሠረት ለማልማት አቅም ማሳያ ማቅረብ ሲችል ነው።

፬/ቅድሚያ የማልማት መብት የሚሰጥበት ዝርዝር ሁኔታ እና አቅም ማሳያ መጠንና የጊዜ ገደብ በደንብ ይወሰናል።

**፰.መሬት የሚለቀቅበት ሥርዓት**

፩/የከተማ አስተዳደር ወይም የወረዳ አስተዳደር መሬት ሲያስለቅቅ መከተል ያለበት ቅደም ተከተል፡-

ሀ)ተነሺዎች ከመነሳታቸው ቢያንስ ከአንድ ዓመት በፊት ስለልማቱ ዓይነት፣ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደት በማወያየት እንዲያውቁት ማድረግ አለበት።

ለ)በዚህ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሰው ቢኖርም የሚመለከተው የፌደራል ወይም የክልል መንግሰት ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ፋይዳ ላለው ለአስቸኳይ ልማት መሬት እንዲለቀቅ

**6. Powers to Clear Landholdings**

The City or Woreda administration has the power to order evacuation and takeover land decided to be expropriated for public purpose under Article 5 of this proclamation.

**7. Giving Priority Rights to Develop Land for the Landholders**

1/ Landholders whose holdings are within the urban area to be redeveloped shall have priority rights to develop their land according to the plan either individually or in a group.

2/ Rural landholders for Agricultural use shall have priority rights to develop their landholdings according to land use plan either individually or in groups.

3/ Priority Rights to develop Land as per sub Article 1 and 2 of this Article will be preserved for the Landholders, when the capacity to develop the land as per the plan is presented.

4/ The details of the the right to develop first and the extent of the capacity to develop, and the time frame shall be determined by a Regulation.

**8. Procedure of the Landholding Handover**

1/The City or Woreda Administration shall follow the following orders when land holders hand over their lands:

a) shall consult land holders who are to be displaced at least one year before they handover their holdings on the type; benefits and general process of the project.

b) notwithstanding to paragraph (a) of this Article, land holders who are to be displaced may be consulted on the type; benefits and general process of the project in less than one year if the concerned Federal or

ከወሰነ ተነሺዎች ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ስለልማቱ አይነት፣ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደት በማወያየት እንዲያውቁት ሊደረግ ይችላል።

ሐ) እንዲለቀቅ በተወሰነው ቦታ ላይ ከሚገኙ ተነሺዎች ወይም ሕጋዊ ወኪሎች የባለመብትነት ማስረጃ እና ካሣ የሚከፈልባቸውን ንብረቶች የልኬትና የመጠን መረጃ መሰብሰብ አለበት። ተነሺዎች ስለልማቱ እንዲያውቁት ከተደረገ በኋላ የተጨመሩ ማናቸውም ንብረቶች ካሳ አይከፈልባቸውም።

መ)በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሐ" መሠረት የተሰበሰበውን መረጃ አጣርቶ ለልማት ተነሺ የሚሰጥ መብት ተጠቃሚነት ይወስናል፣ የካሣ መጠኑንም አስልቶ ካሣና ሌሎች ተያያዥ መብቶችን ክፍያ ይከፍላል።

ሠ)ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ በተወሰነው ቦታ ላይ ለሚገኝ ተነሺ ወይም ሕጋዊ ወኪል የሚገባውን የካሣ መጠን እና/ወይም ምትክ ቦታ ስፋትና አካባቢን ወይም ቤት በመግለጽ በጽሁፍ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት አለበት።

ረ) የሚለቀቀው ይዞታ የመንግሥት ቤት የሰፈረበት ከሆነ የማስለቀቂያ ትዕዛዙ የሚደርሰው ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል እና ቤቱን ለተከራየው ሰው ይሆናል።

ሰ) ተነሺን ከቦታው ማስነሳት የሚችለው ለተነሺው ካሣ ከከፈለ እና ምትክ ቦታ ወይም ቤት ከሰጠ በኋላ መሆን አለበት።

ሸ) መሬት የማስለቀቅ ስርዓት ዝርዝር አፈጻጸሙ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

፪/ተነሺ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ባለመብትነቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ወይም ሠነድ በገጠርም ሆነ በከተማ መሬት የማስተዳደር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በሚያወጣው መርሐ-ግብር መሠረት ማቅረብ አለበት።

Regional State decides that the land is required urgently for investment.

c) Collect landholding rights and conduct inventory, amount and size of all compensable properties from displaced people or their legal representatives whose landholdings are determined to be expropriated. Proprerties added after the expropriateion notification is given to the land holder are not compensated.

d) Decide the legal rights of the holders by checking the authority of the documents collected as sub article 1 (c) of this article,calculate,determine,and pay the amount of the compensation and other related rights,

e) Notify the land holder or his agent in writing to hand over the land expropriated for public purpose with the description of the amount of compensation the landholder shall be paid; and/or the size and location of the land or house in kind compensation.

f) Where the building is state owned the order for handing over shall be given to the Housing Administration Authority and to the lessee.

g) Pay compensation or provide substitute land before the displacement of people from their landholding.

h) The details of expropriation of landholdings procedure shall be provided in a Regulation to be enacted to implement this Proclamation.

2/ Landholders or their agents whose landholdings are to be expropriated shall submit landholding certificates or other proofs that show their landholding rights over the lands that is decided to be expropriated to the urban or rural land administration office on the time schedule of the office.

፫/ተነሺው የካሣ ግምት በጽሁፍ እንዲያውቅ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ:-

ሀ) በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ተገቢው ካሣ ካልተከፈለው በመሬቱ ላይ ከቋሚ ተክልና ግንባታ በስተቀር ሌሎች ሥራዎችን መስራት ይችላል።

ለ) በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ተገቢው ካሣ ካልተከፈለው በመሬቱ ላይ ማንኛውንም በፕላን የሚፈቀድ እና ቀጣይ የቦታውን የልማት ወጪ በመንግስት ላይ የማያዛባ ሥራ መስራት ይችላል፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" መሰረት የተሰራ ሥራ ወይም የተደረገ ለውጥ በካሣ ስሌቱ ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት።

፬/ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ባለይዞታ ትዕዛዙ በደረሰው በ፴ (ሰላሳ)ቀናት ውስጥ ካሣ እና ምትክ ቦታ ወይም ቤት መውሰድ አለበት።

፭/ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ውስጥ የካሣ ክፍያውን ካልወሰደ በከተማው ወይም በወረዳው አስተዳደር ስም በሚከፈት ዝግ የባንክ ሂሳብ እንዲቀመጥለት ይደረጋል።

፮/ ለባለይዞታ የሚሰጠው የመልቀቂያ የጊዜ ገደብ ካሣና ምትክ ቦታ ከተቀበለ ወይም ካሣው በዝግ ሂሳብ ከተቀመጠበት ቀን ጀምሮ ከ ፩፻፳ (አንድ መቶ ሀያ) ቀናት መብለጥ የለበትም።

፯/ በሚለቀቀው መሬት ላይ ሰብል፣ ቋሚ ተክል ወይም ቋሚ የሆነ ሌላ ንብረት ከሌለ ባለይዞታው የልማት ተነሽ ካሣ ከተከፈለው በኋላ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ይዞታውን ለከተማ ወይም ለወረዳ አስተዳደር ማስረከብ አለበት።

፰/በሕገ-ወጥ መንገድ በተያዘ ቦታ ላይ ለሰፈረ ንብረት ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ ለ፴ (ሰላሳ) ቀናት የሚቆይ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ እንዲለቀቅ ይደረጋል።

3/ As of the date of notification in writing on the amount of compensation, the landholder may:

a/ Plant seasonal crops and start other activities on the land other than perennial crops and buildings where the compensation is not paid within three months of the notice on the amount of compensation.

b) Begin developing any kind of activity approved by the plan and does not affect the government's ongoing cost of development of the site where compensation is not paid within six months of the notice on the amount of compensation.

c) Property developed or any change made under sub articles (a) and (b) of this Article shall be included in the valuation for compensation.

4/ Land holder who is served with notice to handover his landholding shall take the compensation and replacement plot or house within 30(thirt) days of notice.

5/ Where the land holder who is served with notice fails to comply with the order within the time prescribed under sub article 4 of this Article, the compensation payment shall be deposited in the closed bank account of the city or Woreda Administration.

6/ The land holder may be forced to handover the land within 120 (one hundred and twenty) days of the payment in cash or in kind compensation; or after the cash is deposited in the bank.

7/ Where there is no permanent property or crop on the expropriated land, the land holder shall hand over his landholding within 30 (thirty) days of the payment of compensation to the City or Woreda Administration.

8/ Where the land expropriated is under illegal occupation, the occupant shall evacuate without claim for compensation within 30 (thirty) days of notice.

፱/የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ባለይዞታ ወይም ባለንብረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) እና (፯) በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያለ በቂ ምክንያት መሬቱን ካላስረከበ የከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደሩ መሬቱን በራሱ ይረከባል። አስፈላጊም ሲሆን ለመረከብ የፖሊስ ኃይል ትብብር ሊጠይቅ ይችላል።

9/Where the landholder fails without justifiable reason ,to hand over his landholding within the time prescribed under sub articles 6 and 7 of this article, the City; or Woreda Administration can take over the expropriated land directly, and as may be necessary,may ask cooperation of the police force.

## ፱. መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ኃላፊነት

፩/ መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ለሥራው የሚፈለገውን መሬት መጠንና የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ ውሳኔ የተሰጠበት ማስረጃ ቢያንስ ሥራው ከመጀመሩ ከአንድ ዓመት በፊት ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ማቅረብ አለበት።

፪/መሬቱ ለሕዝብ ጥቅም እንዲውል ሲወሰን የመሬት ይዞታቸውን እንዲለቁ ለሚደረጉ ባለይዞታዎች የሚከፈለውን ካሣ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ ወጪ እንዲሸፍን ከተወሰነ ገንዘቡን ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ገቢ ያደርጋል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ገንዘቡ ገቢ ተደርጎ ለተነሺዎች ካልተከፈለ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር መሬት አያስለቅቅም።

## 9. Responsibilities of the Land Requiring Body

1/ Land Requiring Body shall submit to the City or Woreda Administration the decision that shows the size and exact location of the land to be expropriated at least one year before the commencement of the project.

2/ Pay the money required for compensation and resettlement to the City or Woreda Administration, when it is decided that compensation and resettlement payment shall be made to thedisplaced people.

3/City or Woreda Administration shall not require handing over of the land until payments are made to landholders who may be displaced as per sub-article 2 this Article.

## ፲. የአገልግሎት መስመሮች ስለሚነሱበት ሥርዓት

፩/የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር በሚለቀቀው መሬት በላይ ወይም በታች የአገልግሎት መስመር መኖር አለመኖሩን የአገልግሎት መሥመር ባለቤት ለሆኑ ተቋማት ምላሽ እንዲሰጡበት በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

## 10. Procedure for Removal of Utility Lines

1/ The City or Woreda Administration shall request in writing utility line owner organizations to reply if they have utility lines over or under ground on the land to be expropriated.

፪/በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ ፩ መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ተቋም ንብረት ካለው ለሚነሳው ንብረት ካሣ እውቅና ባለው ገለልተኛ ገማች በማስተመን ከነዝርዝር ማስረጃው ጥያቄው በደረሰው በ፴ (ሰላሳ) ቀን ውስጥ በጽሁፍ ለጠያቂው አካል ይልካል።

፫/የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ግምቱ በደረሰው በ፴(ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ለባለንብረቱ የንብረቱን ግምት ካሣ ይከፍላል።

፬/የአገልግሎት መስመሩ ባለቤት ክፍያው በተፈጸመለት በ፷ (ስልሳ) ቀናት ውስጥ ካሣ የተከፈለበትን የአገልግሎት መስመር አጠናቆ ማንሳትና መሬቱን መልቀቅ አለበት።

፭/የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፬ እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት መስመሩ ባለቤት ክፍያው በተፈፀመ በ፩፻፳ (አንድ መቶ ሀያ) ቀናት ውስጥ ውስብስብነት ያላቸውን የመሰረተ ልማት መስመሮች አጠናቆ ማንሳትና መሬቱን መልቀቅ አለበት።

፮/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፬ እና ፭ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ልማቱ ካልተነሳ በአንቀፅ ፰ ንዑስ አንቀፅ ፱ መሰረትበማስነሳት ይዞታው የሚወሰድ ሲሆን በወቅቱ ተገቢውን ስራ ያልተወጣ የመሰረተ ልማት ተቋም ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የካሣ አወሳሰን፣ ምትክ አሰጣጥ እና መልሶ ማቋቋም</u>

### <u>፲፩.ለሕዝብ ጥቅም መሬት ሲለቀቅ ለተነሺዎች ስለሚከፈል ካሣ</u>

ለሕዝብ ጥቅም መሬት እንዲለቀቅ ሲደረግ

2/ The organization that has utility lines on the expropriated land shall estimate the value of the utility line to be affected and send it with evidence to the City or Woreda Administration that requested it under sub article 1 of this Article within 30 (thirty) days of receiving the request.

3/The city or Woreda Administration shall pay the compensation within 30 (thirty) days of receiving the estimated cost of the utility lines to the owner organization under sub article 2 of this article.

4/ The utility line owner shall remove utility lines and clear the land within 60(sixty) days after the payment has been made.

5/ Notwithstanding to sub Article (4) of this Article, the utility line owner shall remove complex utility lines and clear the land within 120 (one hundred and twenty) days after the payment has been made.

6/ If the development is not cleared with in the time frame set pursuant to sub article 4 and sub artice 5 of this Article,it shall be cleared and expropriated as per sub Article 9 of Article 8.The Institution of the Infrastructure that failed to discharge its responsibility shall be liable for the damage incurred due to this.The details shall be determined by a Regulation.

## **<u>PART III</u>**

## **<u>DETERMINATION OF COMPENSATION, SUBSTITUTION AND RESETTLEMENT</u>**

### **11. <u>COMPENSATION TO BE PAID TO LAND HOLDERS WHERE LAND IS EXPROPRIATED FOR PUBLIC PURPOSE</u>**

Where land is expropriated for public purposes

ለተነሺው ባለው የንብረትና የይዞታ መብት መሠረት የንብረት እና የልማት ተነሽ ካሣ ይከፈላል።

compensation for the property and displacement shall be paid to the landholders.

**፲፪.የንብረት ካሣ**

፩/የመሬት ይዞታን እንዲለቅ የሚደረግ ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ላደረገው ቋሚ ማሻሻያ ካሣ ይከፈለዋል።

፪/በሚለቀቀው የመሬት ይዞታ ላይ ለሰፈረው ንብረት የሚከፈል ካሣ ንብረቱን ለመተካት የሚያስችል ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሚነሳው ቤት የሚከፈለው አነስተኛ የካሣ መጠን እንደየክልሉ፤እንደአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ተጨባጭ ሁኔታ ወይም ክልሉ፤ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ አስተዳደር በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ቢያንስ ዝቅተኛውን የቤት ደረጃ ሊያስገነባ የሚችል መሆን አለበት።

፬/ በመሬት ይዞታው ላይ ለተደረገ ቋሚ ማሻሻል የሚከፈል ካሣ በመሬቱ ላይ የዋለውን ገንዘብና የጉልበት ዋጋ የሚተካ ክፍያ በአካባቢው ወቅታዊ ዋጋ ተሰልቶ ይሆናል።

፭/ንብረቱ ከሚገኝበት ስፍራ ወደ ሌላ አካባቢ ተዛውሮ እንደገና ሊተከልና አገልግሎት ለመስጠት የሚችል ከሆነ የማንሻ፣ የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ ወጪ የሚሸፍን ካሣ መከፈል አለበት።

፮/ የተለያዩ ንብረቶች የሚሰሉበት የካሣ ቀመር እና ዝርዝር አፈፃፀማቸው በደንብ ይወሰናል።

**፲፫.ስለ የልማት ተነሽ ካሳ እና ምትክ ቦታ**

፩/በቋሚነት ስለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ ካሳ እና ምትክ ቦታ:-

ሀ)የመሬት ይዞታውን በቋሚነት እንዲለቅ

**12. Property Compensation**

1/ The landholder whose land is expropriated shall be paid compensation for the property on the land and the permanent improvement made on the land.

2/The amount of compensation for the property on the land shall cover the cost of replacing the property anew.

3/ Without prejudice to sub article 2 of this Article, the minimum compensation payable to a housing unit, may not, in any way, be less than the current cost of constructing a house per the standard or on the basis of the objective conditions of each Regional State, Addis Ababa and Dire Dawa City Administration.

4/Compensation for permanent improvement to land shall be equal to the current value of capital and labor expended on the land.

5/Where the property on the land can be relocated and continue its service as before, the cost of removing, transporting, and erecting the property shall be paid as compensation.

6/ Valuation methods to determine compensation for various properties and detail prescriptions applicable thereto shall be provided for by a Regulation.

**13.Displacement Compensation and Land Substitution**

1/ Displacement compensation and land substituttion for Rural Landholders permanently displaced:

a) a landholder who is to be diplaced permanently shall

የሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ እንደአከባቢው ሁኔታ ከተወሰደበት መሬት ተመጣጣኝ ምርት የሚያስገኝ ምትክ መሬት የሚገኝ ሲሆን ምትክ መሬት ይሰጠዋል።

ለ)በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" መሠረት ተመጣጣኝ ምትክ መሬት የሚሰጠው ከሆነ መሬቱን ከመልቀቁ በፊት በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ በየዓመቱ ከመሬቱ ሲያገኝ ከነበረው ከፍተኛውን የአንድ ዓመት ገቢ በወቅታዊ ዋጋ ተሰልቶ የልማት ተነሽ ካሳ ይከፈለዋል፤

ሐ)በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" መሠረት ተመጣጣኝ ምትክ መሬት የማይሰጠው ከሆነ መሬቱን እንዲለቅ ከመደረጉ በፊት በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ ከመሬቱ ሲያገኝ የነበረውን ከፍተኛ ዓመታዊ ገቢ በአስራ አምስት ተባዝቶ የልማት ተነሽ ካሳ መከፈል አለበት።

መ)ከመኖሪያ ቦታው የሚነሳ ከሆነ ክልሉ፤አዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተማ አሰተዳደሮች በሚያወጡት መመሪያ የሚወሰን ምትክ ቦታ እና የልማት ተነሽ ድጋፍ መከፈል አለበት።

ሠ) በጊዜያዊነት ለሚለቀቅ መሬት የሚከፈል የልማት ተነሽ ካሣ በማንኛውም ሁኔታ በዘላቂነት ከሚከፈል የልማት ተነሽ ድጋፍ መብለጥ የለበትም።

ረ) የዚህ ንዑስ አንቀፅ ዝርዝር አፈፃፀም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

፪/ በጊዜያዊነት ስለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ የልማት ተነሽ ድጋፍ ካሳ:-

ሀ)ይዞታውን ለተወሰነ ጊዜ እንዲለቅ ለሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱ ከመለቀቁ በፊት በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ ያገኘው ከፍተኛ ዓመታዊ ገቢ መሬቱ እስከሚመለስ ድረስ ባለው

be substitute for a reasonable proportion of the land taken from the area, shall be given a substitute land if it is available.

b) Where equivalent substitute land is given as per paragraph (a) of this sub article, calculated by the current price the land holder shall be paid a one year landholding compensation income which is equal to the highest income he annually used to generate in the last three years preceding the expropriation of the land.

c) Where equivalent substitute land as per paragraph (a) of this sub article is not available, the land holder shall be paid displacement compensation which is equivalent to fifteen times the highest annual income he generated during the last three years preceding the expropriation of the land.

d) Where the landholder is to be displaced from his residence, land for building houses shall be given; and displacement assistance determined by Directives to be issued by Regional States, Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations shall be paid.

e) The amount of compensation given to the temporarily dispalced people shall not be greater than the amount of compensation given to permanently displaced people.

f) Implementation of this sub article shall be determined by a Regulation to be enacted to implement this Proclamation.

2/ Displacement compensation for temporarily displaced Rural landholders :

a) a rural landholder whose landholding has been provisionally expropriated shall, be paid displacement compensation for lost income based on the highest annual income secured during the last three years preceding the

ጊዜ ታስቦ የልማት ተነሽ ድጋፍ ካሣ ይከፈለዋል።

ለ)በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" የሚከፈለው የልማት ተነሽ ካሣ መሬቱ የነበረውን ምርታማነት ለመመለስ የሚወስደውን በአካባቢ የግብርና ተቋም የሚወሰን ተጨማሪ ጊዜ ታሳቢ ማድረግ አለበት።

ሐ)መሬቱ ተመልሶ በፊት ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት መስጠት የማይችል ከሆነ በቋሚነት እንደለቀቀ ተቆጥሮ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሰረት የልማት ተነሽ ካሳ ወይም ምትክ ቦታ ይሰጠዋል፤

መ)መሬቱ በጊዜያዊነት በተለቀቀበት ጊዜ የተከፈለ የልማት ተነሽ ካሣ በዚህ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሐ" መሠረት በቋሚነት እንዲለቀቀ ተቆጥሮ ከሚከፈል ካሳ ተቀንሶ ለተነሺው ልዩነቱ ይሰጠዋል።

ሠ)በጊዜያዊነት ለሚለቀቅ መሬት የሚከፈል የልማት ተነሽ ካሣ በማንኛውም ሁኔታ በዘላቂነት ከሚከፈል የልማት ተነሽ ካሣ መብለጥ የለበትም።

ረ)የዚህ ንዑስ አንቀፅ ዝርዝር አፈፃፀም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

**፫/ስለወል ይዞታ የልማት ተነሺ ካሣ**

በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ለሚለቀቅ የወል ይዞታ የልማት ተነሽ ካሣ ስሌት እና አከፋፈል ሁኔታ ክልሉ፤አዲስ አበባ፤ድሬዳዋ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ መመሪያው ሲወጣ፡-

ሀ)ለተወሰደው የወል መሬት የልማት ተነሽ ካሣ ስሌት የወል መሬቱ ይሰጥ የነበረውን ጥቅም ወይም ጥቅሙ የቀረባቸውን የአኗኗር ዘይቤ ወይም መተዳደሪያ መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል።

expropriation of the land until repossession of the land.

b) Displacement compensation paid under paragraph (a) of this sub article shall take in to consideration the amount of additional time necessary for the land to regain its productivity which shall be determined by the surrounding Agricultural Institution.

c) If the land fails to to serve as before,it shall be consided as expropriated permanently and pursuant to sub article 1 of this article, either a displacement compensation or substitute land shall be given to the land holder.

d) The displacement compensation paid for temporary expropriation under sub-article (1) of this Article, shall be deducted from payment of compensation paid for the land considered as permanently expropriated and the difference shall be paid to the land holder.

e) Displacement compensation for temporary expropriation shall not in any way exceed to the amount of compensation payable to permanent displaced compensation.

f) The detail implementation of this sub-article shall be provided in a regulation to be enacted to implement this Proclamation.

**3/Displacement Compensation for Communal Landholding**

The valuation method and manner of payment to permanent and temporary expropriation of communal land holdings shall be determined in a directive to be issued by Regional States, Addis Ababa, Dire Dawa City Administrations and shall take the following into consideration:

a) Valuation of displacement compensation for communal landholding shall be based on the use of the communal land; or the lost benefits and livelihood of the displaced People.

ለ) የወል መሬቱ ተጠቃሚዎች በግልጽ መለየት አለበት።

ሐ)በወል መሬቱ ላይ የሚገኙ የግልና የወል ንብረት መለየት አለበት።

መ)የወል መሬት በመወሰዱ ምክንያት በካሣ የተገኘውን ገንዘብ ለማህበረሰቡ አባላት እኩል ሊከፈል ወይም በዓይነት ሊጠቀሙበት የሚችሉበትን መንገድ መቅረጽ አለበት።

**፬/በቋሚነት ስለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ ልማት ተነሽ ካሳ እና ምትክ ቦታ**

የከተማ መሬት ባለይዞታ ከይዞታው በቋሚነት ተነሺ በሚሆንበት ጊዜ የሚከፈለው የልማት ተነሽ ካሣ እና የሚሰጠው ምትክ ቦታ በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡-

ሀ) በቋሚነት ለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ ምትክ ቦታ ወይም መኖሪያ ቤት በግዥ እንዲያገኝ ይመቻቻል።

ለ) የሚሰጠው ምትክ ቦታ ከሆነ በቦታው ቤት እስኪገነባ ለሁለት ዓመት የሚኖርበት ቤት ያለኪራይ ይሰጠዋል ወይም ለፈረሰበት ቤት በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ የሁለት ዓመት የልማት ተነሽ ካሣ ይከፈለዋል።

ሐ) የሚሰጠው ምትክ ቤት ከሆነ ለፈረሰበት ቤት በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ የአንድ ዓመት የልማት ተነሽ ካሣ ይከፈለዋል።

መ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ “ለ” እና “ሐ” የሚከፈል የልማት ተነሽ ካሣ መጠን ቢያንስ የአካባቢውን ዝቅተኛ የቤት ኪራይ ለመከራየት ከሚያስችል ያነሰ መሆን የለበትም።

b) Members of the community using the communal land shall be clearly identified.

c) Private and communal property on the expropriated communal land shall be identified.

d) The method of allocating the displacement compensation money or the use of it in kind to all members of the communal landholding community shall be clearly determined.

**4/ Displacement compensation and substitute land for Urban Landholders Permanently Displaced**

Where urban landholders are permanently displaced as a consequence of land expropriation, the valuation of the displacement compensation and substitute land given to them shall be as follows:

a) Landholders permanentlydisplaced shall be provided with substitute land for building houses; or an arrangement shall be made to let them purchase housing units;

b) Where substitute land is provided, a residential house shall be given to the displaced for two years free of charge until he constructs his residential housing or displacement compensation equal to two years housing rentals estimated on the basis of the rental market comparable to the house of the displaced shall be paid;

c) Where a substitute house is provided, the displaced shall be paid a one year displacement compensation equivalent to current rental price of the demolished house;

d) Displacement compensation payable under paragraph (b) and (c) of this sub-article shall not be less than the amount necessary to lease the lower standard housing in the area.

ሠ)ተነሺዎች በነበሩበት አካባቢ ለነበራቸው የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና ለሚደርስ የሥነ-ልቦና ጉዳት ማካካሻ ይከፈላቸዋል። መጠኑ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤

ረ)የሚለቀቀው የሊዝ ይዞታ ከሆነ የሚሰጠው ምትክ ቦታ ከተለቀቀው መሬት በደረጃ እና በስፋት ተመጣጣኝ መሆን አለበት።ይህንን ለመፈፀም የማይቻል ከሆነ አማራጭ የአፈፃፀም ሁኔታ እንደየከተሞቹ ተጨባጭ ሁኔታ በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

ሰ) የምትክ ቦታ ወይም ቤት አሰጣጥ፣ የልማት ተነሽ ካሣ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዝርዝር አፈፃፀም ክልሎች፤አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳሮች በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል።

**፭/በጊዜያዊነት ስለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ የልማት ተነሽ ድጋፍ፡-**

ሀ) በጊዜያዊነት ለሚነሳ የከተማ ባለይዞታ ተነስቶ ለሚቆይበት ጊዜ ምትክ ቤት ወይም በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ ተመጣጣኝ ቤት የሚከራይበት ክፍያ እንዲያገኝ ይደረጋል።

ለ)የከተማ ባለይዞታዎች በጊዜያዊነት በመነሳታቸው ምክንያት ላጡት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ካሳ ይከፈላቸዋል፤

ሐ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ዝርዝር አፈፃፀም ክልሎች፤አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ አስተዳደ ሮች በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል።

**፲፬.<u>ገቢ በመቋረጡ ስለሚከፈል የኢኮኖሚ ጉዳት ካሣ</u>**

፩/ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ቦታ እንዲለቀቅ ከመደረጉ ጋር በተያያዘ ከይዞታው ሳይነሳ በጊዜያዊነት ወይም በዘላቂነት ሲያገኝ የነበረው

e) Displaced People shall be compensated for the breakup of their social ties and moral damage they suffer as result of the expropriation.The amount of compensation shall be determined by the regulation to be enacted to implement this Proclamation.

f) Where the expropriated land is under leasehold, the substitute land to be given shall be equivalent to the expropriated land in standard and size. If it is not possible to do this, the alternative operating situations shall be determined by a directive depending on the situation of the cities.

g) Provision of substitute land or house, displacement compensation and related matters shall be determined in directives that may be issued by Regional States, Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations.

5/**Displacement Assistance to Temporarily Displaced Urban Landholders:**

a) Urban land holders' temporarilydisplaced shall be provided with substitute housing or compensation to lease a house equivalent to the current rental market of the expropriated house for the period till they displaced.

b) Urban land holders shall be paid compensation for the economic loss they suffer due to temporary displacement.

c) The details of this sub-article shall be determined by a Directive to be issued by Regional States, Addis Ababa, and Dire Dawa City Administrations.

**14. <u>Compensation paid for Economic Loss of Income</u>**

1/ a person who lost economic benefit either permanently or temporarily without being displaced as a consequence of land expropriation shall be paid compensation; the person entitled for the compensation, type and amount of

ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለተቋረጠበት ሰው የጉዳት ካሳ የሚከፈል ሲሆን ካሳው ስለሚገባው ተጎጂ እና የጉዳት ካሣው መጠንና አይነት ክልሉ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤

፪/በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ ፩ መሠረት የካሳዉን መጠንና ዓይነት ለመወሰን ከመቀጠር፣ ከንግድ፣ ከኪራይ ከእርሻ ውጪ መሬትን በመጠቀም የሚገኝ ገቢ እና የመሳሰሉ ዓመታዊ የተጣራ ገቢን ታሳቢ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**፲፭.ከገጠር ወደ ከተማ ለተካለለ የከተማ አካባቢ ባለይዞታ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ስለመወሰን**

፩/ ከገጠር ወደ ከተማ በተካለለ የአርሶ አደር ይዞታ ከመኖሪያ ቤቱ ለሚነሳ ባለይዞታ በክልሉ፤በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ካቢኔ የሚወሰን ሆኖ የከተማውን ስታንዳርድ በመጠበቅ ከ፭፻ (አምስት መቶ)ሜትር ካሬ ያልበለጠ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ መሰጠት አለበት።

፪/ዕድሜው ፲፰ ዓመትና በላይ ለሆነው የባለይዞታውን ገቢ በመጋራት አብሮ የሚኖር አርሶ ወይም አርብቶ አደር ልጅ የቦታ ስፋቱ የከተማውን አነስተኛ የመሬት ይዞታ ደረጃ የሆነ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ መሰጠት አለበት።

፫/የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም ለመኖሪያ የሚሰጠው ጠቅላላ የቦታ መጠን ከነበረው የመኖሪያ ይዞታ በላይ መሆን የለበትም።

፬/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ የተገለፀው የመኖሪያ ይዞታ መጠን የባለይዞታው መኖሪያ ቤት ያረፈበትና የአጥር ግቢውን ይጨምራል።

፭/የዚህ አንቀፅ ዝርዝሩ አፈፃፀም ክልሉ፣አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች

compensation shall be determined by the Directives issued by a Regional States.

2/ Incomes generated from employment, rentals, business and the like net annual income except that of the income genereated from agriculture may be considered for determination of the type and amount of compensation as per sub article 1 of this Article.

**15. Residential Housing for Peri-Urban Landholders Incorporated in to Towns**

1/A peri urban rural land holder whose residence is removed shall be entitled to not more than 500 sq. meters of land for building per the standard of the urban as it is decided by cabinet of the Regional State, Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations.

2/ Child of the displaced,peri urban landholder the age of 18 and above shall be provided with the minimum size of land per the standard of the town or city provided he lives with his parent.

3/ Notwithstanding to sub article 1 of this article, the total land size that is given to him shall not exceed the total residential area of thedisplaced landholder.

4/ Residential area under sub article 3 of this Article includes the area within the perimeter fence of the displaced land holder.

5/ The details shall be determined by a Directive to be issued by the Regional State, Addis Ababa and Diredawa City

በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል።

፲፮. **መልሶ ስለማቋቋም**

፩/ የክልል መንግሥት፤የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደር ለካሣ ክፍያ እና ለመልሶ ማቋሚያ ፈንድ ያቋቁማል፤

፪/ ክልሎች፤አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ተነሺዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም የሚያስችል ማቋቋሚያ ማዕቀፍ የመቅረጽ ግዴታ አለባቸው።

፫/የከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደር በተቀረፀው ማቋቋሚያ ማዕቀፍና በሚመደበው ማስፈጸሚያ በጀት ተነሺዎችን የማቋቋም ግዴታ አለበት፤

፬/በገጠርም ሆነ በከተማ ለሕዝብ ጥቅም መሬት የሚለቀቀው ለኢንቨስትመንት ከሆነ ተነሺዎች ከኢንቨስትመንቱ የሼር ባለቤት ሊሆኑ ይችላሉ።

፭/በገጠርም ሆነ በከተማ የልማት ተነሺ በሼር ለመጠቀም ፍላጎት ኖሮት ባለሀብቱ ይህንን ለማድረግ የሚያስችለው ሁኔታ ካለ ባለሀብቱ ለተነሺዎች የኢኮኖሚ አስቻይ ተለዋጭ መፍትሄ በተነሺው፤በባለሀብቱ እና በአስተዳደሩ መሰጠት አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

፮/ /የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕቀፍ ይዘትና ዝርዝር አፈፃፀም በደንብ ይወሰናል።

፲፯.**ንብረት ስለመገመት**

፩/እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬት ላይ ለሚገኝ ንብረት ካሣ የሚወጣውን አገር አቀፍ ቀመር መሠረት በማድረግ በተመሰከረለት የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ አማካሪዎች ይገመታል።

፪/የካሣውን መጠን የሚገምት የተመሰከረለት የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ አማካሪዎች

Administrations.

16. **Resettlement**

1/Regional States, Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations shall establish fund for compensation payment and rehabilitation.

2/Regional States, Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations shall develop resettlement packages that enable displaced people to sustainably resettle.

3/ Urban or Woreda Administrations shall have the duty to resettle the People displaced on the basis of the resettlement package and allocated budget.

4/ If the land expropriation for public purpose is for investment, the people who are displaced may own shares from the investment.

5/ People who are displaced from urban or rural areas and who lost their income as a consequence of land expropriation for public purpose,and who do not own shares from the investment, economic incentives shall be devised by the beneficiaries,the investor and Administration. The details shall be determined by a Regulation.

6/the contents and detail implementation of the resettlement package shall be determined by a Regulation.

17. **Valuation of Property**

1/Compensation for the Property situated on land to be expropriated shall be evaluated by Certified Private Institution or individual consultant valuators on the basis of a nationally approved valuation method.

2/It shall be evaluated by an Autonomous Government Organization established for that purpose where there is no

ከሌሉ ራሱን የቻለ በመንግሥት በተቋቋመ ተቋም ይገመታል።

፫/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት የካሣውን መጠን የሚገምት ድርጅት ከሌለ የሚለቀቀው መሬት እንደሚገኝበት አካባቢ የሚመለከተው የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ተገቢው ሙያ ያላቸው አባላት የያዘ ገማች ኮሚቴ በማቋቋም የሚገመት ይሆናል።

፬/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የሚቋቋመው ገማች ኮሚቴ ሥራውን የሚያከናውንበት የአሠራር ሥርዓት ክልሉ፤አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል።

፭/የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ ፩፣፪ እና ፫ ቢኖርም የሚነሳው ንብረት የተለየ እውቀት የሚጠይቅ ሲሆን አግባብ ባለው የመንግሥት ወይም የግል ድርጅት ሊገመት ይችላል።

፮/ የሚነሳው ንብረት የመንግሥት መሠረተ ልማት ወይም የአገልግሎት መስመር ከሆነ የካሣ ግምቱ የሚዘጋጀው በንብረቱ ባለቤት ይሆናል።

፯/የካሣ ግምት የሚሰላበት ነጠላ ዋጋ ቢበዛ በየሁለት ዓመቱ መከለስ አለበት።

### ፲፰.<u>አቤቱታ ሰሚ አካል እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ስለማቋቋም</u>

፩/ክልሎች፤አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ለሚቀርብ አቤቱታ አቤቱታ ሰሚ አካል እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቋቋም አለባቸው።

፪/ክልሎች፤አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች አቤቱታ ሰሚ አካል እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አስፈላጊ ነው ብለው በወሰኑት

private certified property valuation organization or individual consultant.

3/ Where the organizations under sub articles 1 and 2 of this article do not exist, it shall be, considering location of the expropriated land evaluated by valuation committee established by the relevant Urban or Woreda Administrations comprising proper professionals.

4/ The working procedures of the valuation committee established under sub article 3 of this article shall be determined by the Directive issued by Regional State, Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations.

5/ Notwithstanding to sub-article 1,2 and 3 of this article, where the property assessed requires special expertise, the valuation may be made by a relevant Government or Private Organization.

6/ Where the property is state owned infrastructure or utility line; the valuation shall be made by the government entity owning it.

7/ The unit price of compensation valuation shall be revised at most every two years.

### 18. <u>Establishing Complaint Hearing Body and Appeal Council</u>

1/ Regional States, Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations shall establish Complaint Hearing Body and Appeal Hearing Council which shall have jurisdiction to entertain grievances arising from decisions under this Proclamation.

2/Regional States, Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations may establish Complaint Hearing Body and Appeal Hearing Council in some of their towns as

ከተሞቻቸው ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡

፫/የአቤቱታ ሰሚ አካል እና የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

**፲፱.** **<u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>**

፩/የመሬት ይዞታ ማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ወይም እንዲለቅ ትዕዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብቴ ወይም ጥቅሜ ተነካብኝ የሚል ማንኛውም ተነሽ ትዕዛዙ በደረሰው በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ አቤቱታውን፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ለሚቋቋመው አቤቱታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፤

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተጠቀሰው አካል የሚቀርብለትን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ለተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

**፳.** **<u>ስለ ይግባኝ</u>**

፩/በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፱ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ፴ (ሰላሳ) ቀን ውስጥ ይግባኝ ለክልል ከፍተኛው ፍርድ ቤት፣ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ይግባኝ ማለት የሚፈልግ ከሆነ ልማቱ እንዳይጓተት ቦታውን አስረክቦ ክርክሩን የመቀጠል መብት አለው፡፡

፫/ተነሺው ንብረቱን በማስረከቡ እና በቅሬታ ምክንያት ካሳውን ባለመውሰዱ ለይግባኙኝ ክርክሩ

deemed necessary.

3/The structure, powers and duties of the Complaint Hearing Body and Appeal Hearing Council shall be determined in a Regulation that shall be enacted to implement this Proclamation

**19. <u>Complaints</u>**

1/Any person who received an order of expropriation of his landholding; or who has an interest or claim on the property to be expropriated may file an application within 30 (thirty) days of service of the order to the Complaint Hearing Body which is established as per sub-article 1 of Article 18 of this proclamation.

2/The body mentioned under sub article 1of this article, after investigating the complaint submitted to it; shall make its decisions within 30 (thirty) days of the filing of the application and notify in written to the parties.

**20. <u>Appeal</u>**

1/ A party who is aggrieved with the decision given under Article 19 sub article 1of this proclamation shall file an appeal to the Appeal Hearing Council within 30 (thirty) days of the receipt of the written notice of the decision thereof.

2/ A party aggrieved with the decision of the Appeal Hearing Council may file an appeal to the Regional High Court in case of Addis Ababa and Dire Dawa city, Federal First Instance Court within 30 (thirty) days of the receipt of the decision in writing.The party who is dissatisfied with the decision has the right to continue his claim, however, for the continuance of the development, he has to surrender his land holdings.

3/If the land holder faces economic loss due to the expropriation and is unble to file an appeal, the

የሚሆን በቂ ገንዘብ ከሌለው እና በዚህ ምክንያት የሚቸገር ከሆነ መንግስት ነፃ የህግ አገልግሎት የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

**፳፩.<u>አቤቱቱ የቀረበበትን ቦታ ስለመረከብ</u>**

፩/የመሬት ማስለቀቅ ትእዛዝ የደረሰው ባለይዞታ በዚህ አዋጅ መሠረት አቤቱታ ያቀረበ ከሆነ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር ቦታውን መረከብ የሚችለው፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት አቤቱታ አቅርቦ ውሳኔው ከፀና እና በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሳያቀርብ ሲቀር፣ ወይም

ለ)በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ ንኡስ አንቀጽ ፪ መሠረት ይግባኙን ሳያቀርብ ሲቀር፣

፪/የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ቢኖርም አቤቱታ የቀረበበትን ቦታ በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘ ቦታ ከሆነ በቦታው ላይ የሰፈሩ ንብረቶች በማውጣት የተሰራ ግንባታ እንዲፈርስ በማድረግ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር መሬቱን መረከብ ይችላል።

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፳፪.<u>የፌደራል ተቋማት ሥልጣንና ተግባር</u>**

በሌላ ሕግ ለሚኒስቴሩ የተሰጠ ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ:-

፩/የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር:-

ሀ)ከተማን የሚመለከቱ የአዋጁ ድንጋጌዎች በከተሞች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

ለ)የከተማ ተነሺዎችን በማቋቋም ሥራ ላይ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሐ)ክልሎች፤አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች

government shall arrange for free legal services.

**21. <u>Taking Over Land under Complain</u>**

1/ If the person who received an order of evacuation of his landholding filed a Complaint application as per this Proclamation, the Woreda or City administration may take over of the land only where:

a) The appeal is affirmed as per article 19 sub-article 1of this proclamation and failed to make an appeal on that decision; or

b) The land holder failed to make an appeal as per Article 20 sub-article 2 of this proclamation.

2/ Notwithstanding to sub-article 1 of this Article where Land under complain is illegally occupied land, the Woreda or Urban Administration may takeover of the land after removing the property, demolishing building on the land.

## <u>Part IV</u>
## <u>Miscellaneous Provisions</u>

**22. <u>Powers and Functions of Federal Institutions</u>**

Without prejudice to powers and functions given to the Ministry under other Laws:

1/ Ministry of Construction and Urban Development shall:

a) Ensure and follow up implementation of provisions of this Proclamation pertaining to Urban in Urban Areas;

b) Support resettlement of displaced people from urban areas;

c) Provide technical and capacity building support to

አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ የቴክኒክና አቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፣

መ)አዋጁን ለማስፈጸም መመሪያዎች በወቅቱ መውጣታቸውን ይከታተላል፣ይደግፋል።

ሠ)በከተማ ማልማት ምክንያት የተነሱ ባለይዞታዎች ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ ጥናት ያካሂዳል፣ ለታዩ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል።

**፪/ የግብርና ሚኒስቴር**

ሀ)የገጠር መሬትን የሚመለከቱ የአዋጁን ድንጋጌዎች በክልሎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

ለ)የገጠር ተነሺዎችን በማቋቋም ሥራ ላይ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሐ)ክልሎች፤አዲስአበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ የቴክኒክና አቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፣

**፳፫.<u>የክልሎች፤የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩/ይህንን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጣውን ደንብ እና መመሪያዎች በክልሉ፤ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ወይም ከተሞች እንዲፈጸሙ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

፪/የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕቀፍ ይቀርጻል፣ ይተገብራል።ይህን ማዕቀፍ የሚተገብር እና የሚመራ ራሱን የቻለ ተቋም ይቋቋማል ወይም ካሉት ተቋሞች ይህንን ሀላፊነት የሚወጣ ይሰየማል፤

፫/ከተሞችና ወረዳዎች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል።

፬/በልማት ምክንያት የተነሱ አካላት ያሉበትን የኑሮ

Regional States, Addis Ababa, and Dire Dawa City Administrations;

d) Follow up and support the issuance of Directives required for the proper implementation of this Proclamation; and

e) Asses the living conditions the holders whose land has been expropriated for public purpose for urban development and provide solutions to problems discovered.

**2/ Ministry of Agriculture shall**

a) Follow up and ensure implementation of the provisions of this proclamation pertaining to rural areas in the Regions.

b) Support resettlement of displaced people from rural areas.

c) Provide technical and capacity building support to Regional States, Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations to enable them implement this Proclamation.

**23. <u>Powers and Functions of Regional States,Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations</u>**

1/ Follow up and ensure the implementation of this Proclamation and the Regulation and Directive enacted under it in Regional States, Addis Ababa Dire Dawa City Administrations;

2/ Develop and implement resettlement packages. An independent entity that implement and govern this framework shall be established or appointed from this institution to bear this responsibility.

3/ provide capacity building support to Urban and Woreda Administrations to enable them implement this Proclamation.

4/ asses the living conditions of the displaced persons and

ሁኔታ ጥናት ያካሂዳል፣ለተለዩ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል።

**፳፬.<u>የወረዳ እና የከተማ አስተዳደር ኃላፊነት</u>**

፩/ተነሺዎችን ስለልማቱ አይነት፣ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደቱ ላይ ግልጽ ውይይት በማድረግ እንዲሳተፉ ያደርጋል፣

፪/መሬት እንዲለቁ ለተደረጉ ባለይዞታዎች ተገቢውን ካሣ ይከፍላል ወይም እንዲከፈል ያደርጋል፣

፫/የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕቀፍን ስራ ላይ ያውላል ፣

፬/ካሣ ተከፍሎበት እንዲለቀቅ በተወሰነ መሬት ላይ የሚገኘውን ንብረት በሚመለከት የተሟላ መረጃ ይይዛል፤

፭/ተነሺ አርሶ እና/ወይም አርብቶ አደሮች ኑሮአቸው እንዲሻሻል የድጋፍና ክትትል ሥራዎችን ይሠራል፤

፮/ተነሺዎችን የተመለከተ መረጃና ማስረጃ አደራጅቶ ይይዛል።

**፳፭.<u>ተጠያቂነት</u>**

በዚህ አዋጅ የተቀመጡ ግዴታዎችን በህጉ አግባብና በወቅቱ ያልተገበረ ማንኛውም ግለሰብ፣ ተቋም እና የተቋም ሀላፊ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል።

**፳፮.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩/የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ያወጣል።

፪/ክልሎች፤ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚወጣ ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ያወጣሉ።

provide solutions to the identified problems.

**25.<u>Responsibility of Woreda and Urban Administrations</u>**

Woreda and Urban Administrations shall:

1/organize consultative meetings with people that are going to be displaced on the type; benefits; and generally the process of the project;

2/Pay or make others pay the compensation to the landholders whose land holdings are expropriated.

3/ Implementing the resettlement packages.

4/Maintain record of the property located on the expropriated land.

5/ Support and ensure the improvement of the livelihood of displaced farmers and pastoralists.

6/Maintain record and evidences relating to the displaced.

**25. <u>Accountability</u>**

Any person, institution and institution who does not implement the provisions of this proclamaition shall be liable under the applicable law.

**26. <u>Power to Issue Regulation and Directive</u>**

1/The Council of Ministers shall issue regulation for the implementation of this Proclamation.

2/ Region states or Addis Ababa or Dire Dawa City Administrations may issue Directives necessary for the proper implementation of this Proclamation and Regulation issued per sub article 1 of this Article.

**፳፯.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ አዋጅ ከመጽደቁ በፊት ክስ ቀርቦባቸው ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በቀድሞው አዋጅ ፬፻፶፭/፩ሺ፱፻፺፯ መሠረት ይስተናገዳሉ።

**፳፰.የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

፩/ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬት የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታዎች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፭/፲፱፻፺፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪/ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**፳፱.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለ ወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**27. Transitional Provision**

Cases pending in a court before the coming into force of this Proclamation shall be disposed under the previous Proclamation No. 455/1997.

**28. Repealed and Inapplicable Laws**

1/ The "Expropriation of Land holdings for Public Purposes and Payment of Compensation Proclamation No. 455/2005 is hereby repealed.

2/ No law, Regulation, Directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

**29. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force as of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this September 23rd day of September, 2019**

**SAHELEWORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**
**REPUBLIC OF ETHIOPIA**